# የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ከፍተኛ ፍርድ ቤት
# በዳኛ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የመጠየቅ ሂደት

**በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የመጠየቅ ሂደት፣ ትዕዛዙን የሰጠው ተባባሪ ዳኛ (Associate Judge) ወይም ማጅስትሬት ዳኛ (Magistrate Judge) መሆኑ ላይ ይወሰናል።**

## በማጅስትሬት ዳኛ ውሳኔ ላይ ይግባኝ እንዴት እንደሚጠየቅ

**የማጅስትሬት ዳኛ** የተወሰኑ ክስ መዝገቦችን፣ አቤቱታዎችን እና ችሎቶ ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ፤ ይህም በዳኖቹ ስልጣን ላይ ተከራካሪ ወገኖቹ የሚስማሙባቸውን ክስ መዝገቦችን ያጠቃልላል። በማጅስትሬት ዳኛ ውሳኔ ላይ ካልተስማሙ፣ ወዲያውኑ ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት አይችሉም።

ይልቁንም፣ **ከዚህ በታች በተጠቀሱት የጊዜ ገደቦች** መሠረት **የዳኝነት ክለሳ አቤቱታ (Motion for Judicial Review)** ማቅረብ አለብዎት አቤቱታው የትኛውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ይግባኝ እንደሚሉ በግልጽ መግለጽ፣ የውሳኔውን የተወሰኑ ክፍሎች መጠቆም እና ለምን ይግባኝ እንደሚሉ ማስረዳት አለበት። በዚህ አቤቱታ ላይ አዲስ ማስረጃ ማቅረብ አይችሉም።

አቤቱታው በተባባሪ ዳኛ (Associate Judge) የሚታይ ሲሆን፣ ዳኛው የማጅስትሬት ዳኛን ውሳኔን ሊያፀድቁ፣ ሊያሻሽሉ ወይም ሊሽሩት ይችላሉ።

ተባባሪ ዳኛው የዳኝነት ክለሳውን ካጠናቀቁ በኋላ፣ በአነስተኛ የገንዘብ ካሣ ጥያቄ ክርክር (small claims case) ላይ ከተሰጠ ውሳኔ በስተቀር፣ በተባባሪ ዳኛው ውሳኔ ላይ ለበለጠ ክለሳ ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

**<u>የዳኝነት ክለሳ አቤቱታ ማቅረቢያ የጊዜ ገደቦች</u>**

(ውሳኔው/ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ይቆጠራል)፡-

- የቤተሰብ ፍርድ ቤት ጉዳዮች (የወላጅነት እና የቀለብ ጉዳዮችን ሳይጨምር)፡- 10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት
- የወላጅነት እና የቀለብ መስጠት ክስ መዝገቦች 30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት
- ሌሎች ሁሉም ክስ መዝገቦች፡- 14 የቀን መቁጠሪያ ቀናት

## በተባባሪ ዳኛ ውሳኔ ላይ ይግባኝ እንዴት እንደሚጠየቅ

በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ከፍተኛ ፍርድ ቤት (Superior Court) ውስጥ በተባባሪ ዳኛ በተሰጠ የመጨረሻ ትዕዛዝ ወይም ክስ መዝገብዎን በሚዘጋ ውሳኔ እና በተወሰኑ የመጨረሻ ባልሆኑ ትዕዛዞች ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለዎት።

ይግባኝ ለማለት፣,ውሳኔው/ትዕዛዙ በወጣ **በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ** ክስ መዝገብዎ ባለበት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዋና ጸሐፊ ቢሮ **የይግባኝ ማስታወቂያ (Notice of Appeal)** ያስገቡ። ስለ አቀራረቡ ሂደት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይሄንን ይጎብኙ፡-

https://www.dccourts.gov/court-of-appeals/how-to-appeal

**አነስተኛ የገንዘብ ካሣ ጥያቄዎች (Small Claims) - ለመጨረሻ ውሳኔዎች ብቻ:** በአነስተኛ የገንዘብ ካሣ ጥያቄ ክስ መዝገብ ላይ በተባባሪ ዳኛ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለመጠየቅ፣ ውሳኔው በተሰጠ በ3 ቀናት ጊዜ  ውስጥ በቀጥታ ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የይግባኝ ፈቃድ ማመልከቻ (Application for Allowance of Appeal) ያስገቡ። ቅጹ በዋና ጸሐፊው ቢሮ እና በዲሲ ፍርድ ቤቶች ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡-
https://www.dccourts.gov/services/forms

# የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ከፍተኛ ፍርድ ቤት
# በዳኛ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የመጠየቅ ሂደት

## በማመልከቻ ማስገባት ሂደት ወይም በቀጣይ እርምጃዎች ላይ እርዳታ ማግኘት ይፈልጋሉ?

እባክዎን ከሰኞ እስከ አርብ፣ ከጠዋቱ 8:30 a.m እስከ ምሽቱ 5:00 p.m.ሰዓት ድረስ ክስ መዝገብዎ የቀረበበትን ቢሮ ወይም የክፍሉን የራስ-አገዝ ማዕከል ያነጋግሩ።

**Civil Actions Branch**
**[የፍትሐብሔር ክሶች ቅርንጫፍ]**

500 Indiana Ave NW, Room 5000

(202) 879-1133

**Landlord and Tenant Branch**
**[የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ]**

510 4th St NW, Room 110

(202) 879-4879

**Small Claims Branch**
**[የአነስተኛ የገንዘብ ካሣ ጥያቄ ቅርንጫፍ]**

510 4th St NW, Room 120

(202) 879-1120

**Criminal Division**
**[የወንጀል ክፍል]**

500 Indiana Ave NW, Room 4000

(202) 879-1373

**Domestic Violence Division**
**[የቤት ውስጥ ጥቃት ክፍል]**

500 Indiana Ave NW, Room 4510

(202) 879-0157

**Family Court Self-Help Center**
**[የቤተሰብ ራስ አገዝ ማዕከል]**

500 Indiana Ave NW, Room JM 570

(202) 879-0096

**Probate Self-Help Center**
**[የውርስ ራስ አገዝ ማዕከል] ቦታ:**

515 5th St NW, Room 318

(202) 508-1681